የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄን
**Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy**
Tel +44 208 1335670 pr @ginbot7.org

ቀን፡ ታህሳስ 26 2001

ጋዜጣዊ መግለጫ

## <u>መለስ በሶማሊያ የደረሰበት ሽንፈትንና የሚያደርገውን ሽሽት በተመለከተ ከግንቦት 7 ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግልጫ</u>

የአንድነት ሊቀመንበር የወ/ት ብርቱካንን፣ የአርቲሰት ቴዲን፣ የኦፍዴን ጸሃፊ አቶ በቀለን፣ ሌላውንም በመሃል ሀገሩና በዳሩ፣ በዘሩ፣ በእምነቱና በፖለቲካ አስተያየቱ የተነሳ የወያኔ አገዛዝ በአስር የወረወረውን፣ ግፍና በደል የሚፈጽምበትን ዜጋ በሙሉ እናስታውስ። በአራቱ የሃገሪቱ ማእዘናት የሚፈሰውን የሲቃ እንባ ለማበስ ሁላችንም በጋራና በሚመስለን፣ አቅማችን በፈቀደ መንገድ ማድርግ የሚገባንን ሁሉ እናድርግ። በሌላ በኩል ግን ከእዚሁ ትግል ጋር አብሮ መሄድ ያለባቸውን ሌሎች ወያኔን ከስር መሰረቱ የሚነቅሉትን ግፍና በደልን ከምንጫቸው የሚያደርቁትን ስራዎቻችንን መስራቱን አንርሳ። ወያኔ የወ/ት ብርቱካንን መታሰር የመርዶ ዜና ለኛ ወርውሮ ለሃገራችን ህዝብ መረጃ የሚያቀርቡ የመገናኛ ብዙሃን፣ ራድዮኖች፣ የመወያያያ ክፍሎች፣ ጋዜጦችና ድረ-ገጾች በእዚህ አሳዣኝ ዜና ላይ ትኩረታቸው በሳቡበት ወቅት ለራሱ ለወያኔ መርዶ የሆነ ዜና የመገናኛ ብዙሃን በቂ ሽፋን ሳያገኝ እንዲያልፍ እያደረገ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባናል። ይህንን አንፍቀድለት።

ወያኔ ዛሬ ከፍተኛ የሽንፈት ቅሌት ተከናንቦ፣ በሽዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ደም የሶማሊያ አሸዋ ጠጥቶት እንዲቀር አድርጎ፤ ወንድም በሆነው የሶማሊያ ህዝብ ላይ እጅግ አሰቃቂ ወንጀል በመፈጸም በሃገራችን ላይ ለዘመናት የማይፋቅና ብሄራዊ ደህንነታችንን በከፍተኛ አደጋ ላይ የጣለ የጥላቻ መርዝ ዘርቶ፣ የብርተካንን የመታሰር ዜና ሽፋን አደርጎ ሶማሊያ ውስጥ እየደነፋ እንዳልገባ ዛሬ ጭራውን በአግሩ መሃል ቆልፎ ተደብቆ እየወጣ ነው።

ለሃገራችን መረጃ የሚያቀርቡ ማናቸውም የመገኛኛ ብዙሃን፣ ስለሃገራችን ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም የሚቆረቆሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና ቡድኖች፣ እንዲሁም በየትኛውም የአለም ክፍል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወያኔ ሶማሊያን በመውረር በሃገራችን ብሄራዊ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት፣ ያባከነው ሃብትና ያጠፋው ህይወት ህያው የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ዛሬ ሃገራችንን በወራሪነት መንፈስ ይዘው የሚገዙት ዘረኞች፣ በሱማሌ ህዝብ ላይ የፈጸሙት የጦር ወንጀል በሃገር ውስጥ ከፈጸሙት የዘር ማጥፋትና የዜጎች ግድያ፣ የሃገር ክህደትና የዘረፋ ወንጀል ጋር ተደምሮ በወንጀል የሚጠየቁበት ሰአት መድረሱን ልናስታውሳቸው ይገባል።

ሲኩራሩበት የነበረ የጦር ጉልበታቸው፣ እንደነሱ በልእለ ሃያል መንግስት የረቀቀና ዘመናዊ የትጥቅ ቀለብ በማይሰፈርለት፣ ነገር ግን ለነጻነቱ ቆርጦ በተነሳ ደሃ ህዝብ ፊት እንደ ጉም እንደበነነ፣ ወያኔዎች አፍነውን ለሚገዙን ለራሳችንም ለእነሱም ልናስታውሳቸው ይገባል። ‹‹ወያኔዎች ሆይ በገዥነት የምትቀጥሉት በሃይላችሁና በጉልበታችሁ ሳይሆን እኛ በቃችሁ ብለን ቆርጠን እስከምንነሳ ብቻ እንደሆነ እወቁት። እጣችሁ እንደምታስቡት በእናንተው እጅ ሳይሆን በእኛ እጅ ነው›› ልንላቸው ይገባል። ከእዚህም ተሻግረን እኛ ዝም ብለን ባናየቸው እንኳን አዲስ አበባ መድረስ ቀርቶ ተከዜን ማለፍ አይችሉ እንደነበር ልናሳያቸው ቃል መግባታችንና መቁረጣችንን ሁላችንም በተግባር ልናሳያቸው ይገባል።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ